በአብክመ የደሴ ከተማ
አስተዳደር እስልምና ጉዳይ
ምክር ቤት

Amhara Region Dessie City
Administration
Islamic Affair Council

Reg.No/ቁጥር: ደከአእጉም/ቤት/911/17
Date/ቀን: 05/13/12/2017

- ለአብክ/መንግስት አስተዳደር፣
- ለአብክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ፣
  ባሕር ዳር፣
- ለደሴ ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ፣
  ደሴ፣

**ጉዳዩ፡-የግዕዝ ትምህርት በአስገዳጅነት በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሰጥ መወሰኑን ስለመቃወም፤**

በአብክመ ትምህርት ቢሮ በቁጥር ትብ2/63/ስት-1 በቀን 13/12/2017 በተጻፈ ደብዳቤ በ2018 የትምህርት ዘመን በክልሉ ባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ የግዕዝ ትምህርት እንዲሰጥ አስገዳጅ ሆኖ ወርዷል።

ነገር ግን ይህ የትምህርት ዓይነት ሙስሊሙን ማህበረሰብ ታሳቢ ያላደረገና ውይይት ያልተደረገበት በመሆኑ፣ እንዲሁም በሕገ መንግስቱ እንዲሰጡ ታሳቢ ካደረጋቸው ትምህርቶች ውስጥ ያልተካተተ ባለመሆኑና የማህበረሰብ ውይይት ያልተደረገበት በመሆኑ በክልላችን ትምህርቱ እንዲሰጥ ፈቃደኛ አለመሆናችንን የሚገልጽ 3(ሶስት) ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር!

عثمان حسين أحمد
كاتب مجلس الشؤون الإسلامية في إدارة مدينة دسي

ግልባጭ፡

- ለአብክመ እስልምና ጉዳዮች ከ/ም/ቤት፣
  ባሕር ዳር፣
- ለደሴ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት፣
- ለደሴ ከተማ አስተዳደር አስ/ብልፅግና ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት፣
- ለደሴ ከተማ አስ/ሰላምና ፀጥታ መምሪያ፣
  ደሴ፣

- ከዚህ በታች ከተራ.ቁጥር 1-12 በገለፅነው መሰረት የግዕዝ ትምህርት የመስጠት ተግባሩ በአስቸኳይ እንዲቆም እየጠየቅን ክልላችን ከተወሰኑ አመታት ወዲህ ብዙ አሳሳቢ ጉዳዩች እያሉበት ሌላ ተጨማሪ ችግሮችን መፍጠሩ ከክልሉ አልፎ እንደሀገርም አሳሳቢ የሚያደርገው ጉዳይ ሲሆን፡-

1. የግዕዝ ትምህርት በርካታ ሀይማኖታዊ አተያዮች ሊኖሩት እንደሚችል እየታወቀ ማህበረሰቡ ሳይወያይበት በአንድ ደብዳቤ በግዳጅ ለማስፈጸም መሞከሩ ተገቢ አለመሆኑ፤
2. የግዕዝ ትምህርት ስነ ጽሁፉ በሙያው ባለቤቶች በዝርዝር እንደተጠናው የሚያተኩረው መጽሀፍ ቅዱስና አዕዋድ፣ የኦርቶዶክስ አባቶች ገድላትና ተዓምራት፤ መልካመልክ (የቅዱሳን፤ የመላዕክትና የመለኮት አካላዊ ገጽታን በኦርቶዶክሳዊ እይታ የሚገልጹ)፣ ክብረ-ነገስት እና ፈትሀ- ነገስት እንዲሁም ልፋፈ ጽድቅ እና እውደ ነገስት አይነት ሙሉ ለሙሉ ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮት ላይ ብቻ ሆኖ ይገኛል። ይህም ማለት የግዕዝ ትምህርት አፈጣጠር እና እድገት እንዲሁም ሞት ከኦርቶዶክስ ክርስትና ጋር ብቻ የተያያዘ ነው ማለት ነው። ስለሆነም በት/ት ቤት ውስጥ ትምህርቱ በሚሰጥበት ወቅት የሚሰጡ ምሳሌዎች፣ የሚወሩ ታሪኮች እና ልጆቹ እንዲያጠኑ የሚነገራቸው ሁሉ ከዚሁ ትምህርት ቀደም ሲል ስራ ላይ ዉሎ በነበረበት አዉድ ላይ የተንጠለጠለ ይሆናል ማለት ነው፤
3. ከላይ የተጠቀሰው ከንድፈ ሀሳብ ትንታኔ አንጻር ሲሆን ግዕዝን በሚያስተምሩ በክልላችን የሚገኙ የከፍተኛ ት/ት ተቋማትም ችግሩ በተግባር በግልጽ ተስተዉሏል። እንዲያውም ግዕዝን አለማዊ ይዘት እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል አይቻልም የሚለው በይፋ መወያያ ሆኖ ወጥቷል፤
4. የግዕዝን ትምህርት በመላ ክልሉ ባሉ ትምህርት ቤቶች ለማስተማር የሚያስችል ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተምሮ እና ተመርቆ የወጣ ብቁ የሰዉ ኃይል እንደሌለ ግልጽ ነው። በከፍተኛ ትምህርት ተቁማት እንኳን በገጠመው የሰው ኃይል እጥረት ትምህርቱን የሚሰጡትን ሰዎች ከቤተ ክህነት ለማምጣት የተገደዱ መሆኑ የሚታይ ሀቅ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የሀይማኖት ሰባኪያን በበቂ ሁኔታ አለማዊ ትምህርት ለማስተማር ስልጠና ሳይወስዱ ከሀይማኖት አስተምህሮ ጋር ብቻ ተያይዞ ለዘመናት የቆየን ትምህርት ህጻናት ልጆቻችንን እንዲያስተምሩ መፍቀድ ልጆቻችን በማንፈልገው ሀይማኖት አስተምህሮ በተዘዋዋሪ እንዲታነጹ ማድረግ ነው ብለን እናምናለን፤

5. የግዕዝ ትምህርት በአብዛኛው ከኃይማኖታዊ ጉዳዮች ውጭ ጥቅም ሊኖረው ይችልላል ከተባለ ባህልን እና ታሪክን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመረዳት ያግዛል የሚል ነው። ይሁን እና የአማራ ሙስሊሞች ቀደም ሲል በነበረው ትምህርት ለሁሉም ተደረሽ ያለመሆን ችግር ምክንያት አባቶቻችን እና እናቶቻችን ታሪክ እና ባህላችንን በመንዙማዎቻቸው፣ ግጥሞቻቸው፣ በተለያዩ ጹሁፎቻቸው በጣም በሰፊው ሰንደው ያስተላለፉልን በአረበኛ ትምህርት እና በአጅም (አማረኛዉን በአረበኛ ፊደላት መጻፍ) ነው። በመሆኑም ከባህል እና ከታሪክ እንዲሁም አገርበቀል የሳይንስ እዉቀት አንጻር የአማራ ሙስሊሞች የደለበ ውርስን ለመረዳት ግዕዝ ምንም አይነት አስተዋጽዖ የማይኖረው ሲሆን በተቃራኒው አረበኛ ብቸኛ እና የማይተካ ሚና አለው። ሀቁ ይሄ ሆኖ እያለ አረበኛ ትምህርት በግል በከፈትናቸው ትምህርት ቤቶቻችን ጭምር እንዳይሰጥ በኃይል ከልክሎ ግዕዝን በግዳጅ በሁሉም ት/ት ቤቶች እንዲሰጥ ማድረግ እጅግ በጣም አድሏዊ እና የለየለት የማግለያ አካሄድ ነው ብለን እናምናለን፤

6. ከሀገራዊው ትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲው እንዲሁም ከአጠቃላይ ትምህርት አዋጁ አንጻር ስናየው ህጻናት በመጀመሪያ ደረጃ ት/ት የአፍ መፍቻ ትምህርትቻቸዉን፣ እንግሊዘኛ እና፣ ከ3ኛ እስከ 8ኛ ደግሞ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የስራ ትምህርት ከሚሆኑት የሀገራችን ትምህርቶች አንዱን በወላጆች እና ተማሪዎች ምርጫ እንዲማሩ የሚደነግግ ሲሆን በዚህ አግባብ ግዕዝ ያለ ውይይት እና መግባባት በአስገዳጅነት የሚሰጥበት አግባብ በፍጹም ህጋዊ ካለመሆኑ ባሻገር ከት/ት ፖሊሲው ጋርም የሚጋጭ ተግባር ነው።

7. አብዛኛው የክልሉ ህጻናት በጸጥታ ችግር ከትምህርት ገበታ ርቀው ባለበት እና የባለፉት ሁለት አመታት ትምህርቶችን በአንድ አመት ለማካካስ በሚል ክልሉ እየለፋ ባለበት አውድ ይሄን አጀንዳ ወደፊት እንደት እንደመጣ ስናይ በቅርቡ የኦርቶዶክስ ኃይማኖታዊ መንግስት ለመመስረት ጥብቅ ትግል እያደረጉ እንደሆነ እና የክልሉን አመራር ጭምር እየተቆጣጠርን ነው፤ አራት ኪሎ እንገባለን ወዘተ እያሉ በግልጽ እየነገሩን ያሉ ሰዎችን ንግግር በአግባቡ እንድናጤን የሚያስገድድ ሆኖ የመጣ ነው።

8. መንግስት ሀይማኖት እና ትምህርት የተለያዩ ናቸው መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም ሃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ አይገባም ተብሎ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 27 እና ሌሎች አንቀፆች ላይ ተደንግጎ እያለ ህገ-መንግስቱን በመተላለፍ ሃይማኖትን በቀጥታ ት/ቤት ላይ ተግባራዊ እንዲሆን የታሰበም ጭምር በመሆኑ በጥብቅ እንቃወማለን።

9. ትምህርት ለህዝበ ሙስሊሙም ሆነ ለሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የሚሰጠው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የሌለው፣ እንዲሁም ከሌሎች ጎረቤት ክልሎችም ሆነ አገሮች ጋር ለመግባባትም ሆነ ለመገናኘት ምንም የማያገለግል ሲሆን እንደውም ይዞት የሚመጣው ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ኪሳራ ከባድ በመሆኑ በፍጥነት እንዲቆም እናሳስባለን።

10. ይህ ትምህርት ሲዘጋጁም ሆነ ሲጠና በስውር እና ሙስሊሙን ማህበረሰብ ባገለለ መልኩ በመሆኑ የኦርቶዶክስ ሃይማኖታዊ አስተምሮን ተግባራዊ ለማድረግ የተፈለገ በመሆኑ በህዝበ ሙስሊሙ ዘንደ ተቀባይነት የለውም ልጆቻችንም አይማሩም

11. የክልሉ መንግስት ጉዳዩን በግርግር እና በችኮላ ለማስፈጸም ከመሞከር ታቅቦ እንደገና እንዲያጤነው እና በትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲው አግባብ የትምህርት ስርዓቱ እንዲመራ እንዲደረግ ፤

12. እነኚህን እና መሰል ችግሮችን እያሳሰብን ከትምህርት ፖሊሲው እና ከአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ አውድ ውጭ ጉዳዩን እንቀጥላለን የሚባል ከሆነ እና በግዳታ ተግባረዊ እናደርጋለን ከተባለ ሃይማኖታዊ ቅኝ ግዛት በመሆኑ የማንቀበል እና ህዝባችንን ይዘን ወደ ሰላማዊ ትግል የምንገባ መሆናችን እንዲታወቅልን በትህትና እንገልፃለን።